ኖቬምበር 2017 QuickNotes ፈጣን የዜና መልእክት ቁ. 2

## የትምህርት ቦርድ የ 2018-2019 የትምህርት ቀን መቁጠሪያ/ካለንደር አጸደቀ።

<Summary:> የትምህርት ዓመቱ የሚጀመረው ማክሰኞ ሴፕቴምበር 4, 2018 ሲሆን የሚጠናቀቀው ሐሙስ ጁን 13, 2019 ላይ ነው።

የትምህርት ቦርድ ለ 2018-2019 የትምህርት ዓመት የሚሆን ቀን መቁጠሪያ/ካለንደር ወስኗል። የትምህርት ዓመት የሚጀምረው ማክሰኞ ሴፕቴምበር 4, 2018 ሲሆን ትምህርት ቤት የመጨረሻው ቀን ሐሙስ ጁን 13, 2019 ይሆናል። ቀን መቁጠሪያው የሚያካትተው፣ 182 የትምህርት ቀኖችን፣ እንዲያጥር የተደረገ /ያጠረ/ የስፕሪንግ እረፍት፣ ለእቅድ ዝግጅት እና የሙያ ማበልፀጊያ የተያዙ ሁለት ቀናት፣ እና ሁለት ከ Rosh Hashanah and Yom Kippur የተገጣጠሙ የሥራ ቀኖችን ነው።

ከስቴት ዋና አስተዳዳሪ ገቨርነር ላሪ ሆጋን (Gov Larry Hogan) የ2016 መመሪያ፤ የትምህርት ዓመት የሚጀምርበትን እና የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ፣ ት/ቤት ከሌበርዴይ /የሠራተኛ ቀን/ቀጥሎ ካለው ማክሰኞ በፊት እንደማይጀምር እና ከጁን 15 አስቀድሞ መጠናቀቅ እንዳለበት ካስተላለፉት መመሪያ ጋር ለማጣጣም፣ በተለምዶ MCPS ከነበረው የስፕሪንግ እረፍት ከአራት-ትምህርት የማይሰጥባቸው ቀኖች ወደ ሁለት ተቀንሷል። በተጨማሪም፣ ከስፕሪንግ እረፍት የተቀነሱት ሁለት ትምህርት የማይሰጥባቸው ቀኖች፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ት/ቤቶች የሚዘጉበትን ቀናት በማስተማር ለማካካስ ይሆናሉ።

የተቀሩት ሁለቱ ትምህርት የማይሰጥባቸው የእቅድ ዝግጅት/የሙያ ማበልጸጊያ ቀናት የሚውሉት ጃኑዋሪ 28 በሁለተኛው ማርክ የሚሰጥበት ወቅት እና ጁን 5 ከኢድ-አልፈጥር ጋር ተገጣጥሞ ነው። የቀን መቁጠሪያው/ካላንደሩ /በሁለት ሰሚስተሮች ከ K-12 ክፍሎች ቀድሞ መለቀቅን ያጠቃልላል።

[ቀን መቁጠርያ/ካላንደሩን ይመልከቱ]()

እዚህ ድረ-ገጽ ላይ የበለጠ መረጃ ይገኛል።
http://www.montgomeryschoolsmd.org/calendar/proposed-calendar-2018-19.aspx

**ሁለት የ MCPS ት/ቤቶች አገር-አቀፍ "National Blue Ribbon" ሽልማት አሸንፈዋል።**

<Summary:> ፋርምላንድ (Farmland) እና ሮናልድ ማክኔይር (Ronald McNair) አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሽልማቱን ለመውሰድ 38ኛ እና 39ኛ የMCPS ት/ቤቶች ሆነዋል።

ይህ በአገር-አቀፍ ደረጃ የከበረ የት/ቤት ሽልማት "National Blue Ribbon School award" ለ ት/ቤቶቹ የተሰጠው በዩ.ኤስ.የትምህርት ዲፓርትመንት (The U.S. Department of Education (USDE)) ነው።**Farmland Elementary SchoolRonald McNair Elementary School** ሁለቱ ት/ቤቶች የሽልማቱን ፕግራም የተከታተሉት ዋሽንግተን ዲ.ሲ በሚገኘው ኦምኒ-ሾርሃም ሆቴል (Omni-Shoreham Hotel in Washington, D.C) ነው። በዚህ ፕሮግራም ከ44 ስቴቶች እና ከዲ.ሲ 342 ት/ቤቶች የከፍተኛ ደረጃ ሽልማት ተካፋዮች ሆነዋል።

በነዚህ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በምንባብ እና በሂሳብ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ከመሆናቸውም በላይ አብዛኞዎቹ ት/ቤቶች በኤኮኖሚ አቅም ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎችን የሚያገለግሉ ናቸው። ከ MCPS ት/ቤቶች ውስጥ ለዚህ ከፍተኛ "National Blue Ribbon Schools" ሽልማት በአሸናፊነት ለመሰየም McNair እና Farmland 38ኛው እና 39ኛው የMCPS ት/ቤቶች ናቸው።

ሁለቱም ት/ቤቶች በዲሴምበር 2016 የሜሪላንድ "Maryland Blue Ribbon Schools" በመባል ተሰይመው ነበር። ይህም ለአገር-አቀፉ "National Blue Ribbon Schools" እንዲታጩ አስችሏቸዋል።

**የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ስትራትሞር "Strathmore" በተባለ ቦታ የሙዚቃ ትርኢቶችን ተመልክተዋል።**

VIDEO /ቪዲዮ/

13,000 የሚሆኑ የ MCPS የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በዚህ ሣምንት ወደ ስትራትሞር የሙዚቃ ማእከል የተጋበዙት "National Philharmonic" በተሰኘ ፕሮግራም አማካይነት ነው። አሁን 13ኛውን ዓመት በያዘው ፕሮግራም፣ ተማሪዎች "Music: It's Element-ary." በተሰኘ ሁሉ-አዲስ ፕሮግራም ለመሳተፍ ችለዋል። በዚህ ወር መግቢያ ላይ፣ ከ 12,000 የሚበልጡ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች በ Strathmore የተካሄደውን "blues and jazz" ፕሮግራም ጎብኝተዋል። በ "Strathmore" የሚካሄዱት የሙዚቃ ትርኢቶች ለተማሪዎች የሙዚቃ ፍቅር እንዲያድርባቸው/ለመገንባት እና በት/ቤቶች የሚማሩትን የሙዚቃ ትምህርት ጽንሰሃሳብ ለማዳበር ይጠቅማቸዋል።

**ኖቬምበር 18 የሚከበረውን የሞንጎመሪ ካውንቲ የታንክስጊቪንግ /የምስጋና መስጫ/ ትርኢት ይሳተፉ።**

<Summary:> 20ኛው የካውንቲ "Thanksgiving parade!"የምስጋና መስጫ ሠልፍ ትርኢት እያምልጦት!
ከ140 በላይ የሰልፍ ትርኢቶች፣ የሙዚቃ ባንድ፣ የቲአትር ስራዎች፣ እና ለታይታ የሚቀርቡ ትላልቅ የተነፋፉ ነገሮች ይገኙበታል።

**ሁሉም ሰው የሰልፍ ትርኢት ይወዳል!**

**የሞንጎመሪ ካውንቲ 20ኛው የታንክስጊቪንግ የሰልፍ ትርኢት** "Thanksgiving Parade" **ቅዳሜ ኖቬምበር 18 ከ10 a.m.–noon on ጀምሮ እስከ እኩለቀን ከዚያም በላይ ይከበራል። በአካባቢው ብቸኛው የ** "Thanksgiving Parade" **ትርኢት ነው። ከ140 በላይ የሰልፍ ትርኢቶች፣ የሙዚቃ ባንድ፣ የቲአትር ስራዎች፣ እና ለታይታ የሚቀርቡ ትላልቅ የተነፋፉ ምስሎች ይገኙበታል። መስመሩ ከ** Ellsworth Drive **እና** Fenton Street, Silver Spring, **ተነስቶ** downtown south **በ** Georgia Avenue **እስከ** Silver Spring Avenue **ይሄዳል።.**

**የሰልፍ ትርኢቱ፤ የኮሌጅ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሰልፈኛ ጓዶችን፣ የሚያብለጨልጩ አንፀባራቂ የታንክስጊቪንግ እና የክርስማስ** "Thanksgiving & Christmas floats" **ተዕይንት ጭነው ከሰልፈኞች ጋር የሚጓዙ መኪናዎች፣ ቲያትራዊ ትዕይንቶች፣ የተለያዩ ባህሎችን የሚያንፀባርቁ የሙዚቃ ጓዶች፣ 12-ጫማ ተነፋፍቶ የሚቆም ተርኪ** "turkey" **(ግዙፍ ከአንገቱ በላይ ያልተሸፈነ የዶሮ ዝርያ) ምስል፣ 12-ጫማ ተነፋፍቶ የሚቆም የወፍ ዓይነት** "penguin"**፣ ሞተር ብስክሌተኞች፣ ያጌጡ ፖሊስ ፈረሰኞች፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ መዝናኛ** "T-Recs" 12-foot dinosaur**፣ የቁንጅና ንግስት፣ የእሳት አደጋ መኪናዎች፣ ጥንታዊ መኪናዎች እና የውሻ ትርኢቶች፣ እና እንስሳትን ከአደጋ የሚከላከሉ ቡድኖችን ጭምር ያካትታል። ዘወትር እንደሚደረገው፣ ትርኢቱ ሲጠናቀቅ** Santa's **ለበዓሉ የተዘጋጀ ሙዚቃ ይጫወታል፣ እና የትእይንት ተሳታፊ/**featuring elves **ለእድምተኞች በሙሉ እሽግ ከረሜላዎችን ይበተናል።የ** ABC7 **ሜትሮሎጅስት ብራያን ቫን ዲ ግራፍ** (Meteorologist Brian Van de Graaff) **እና የ** ABC7 **የትራፊክ ሪፖርተር ጁሊ ወራይት** (traffic reporter Julie Wright) **የመድረክ ዝግጅቱን ይመራሉ።**

**ዝናብ ቢኖርም ባይኖርም ሰልፉ ይቀጥላል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 240-777-0311 ይደውሉ ወይም ይህንን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ፡-**
www.silverspringdowntown.com

**በጎ-ፈቃደኝነት**
**የሞንጎመሪ ካውንቲ የታንክስጊቪንግ ሰልፍ ትርኢት ሁልጊዜም እንደሚደረገው** elves **እና** pilgrims, reindeer **እና** penguins **በመሆን የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞችን ይፈልጋል። በሰልፍ ትርኢት ያሸበረቁ ልብሶችን ለብሰው የአሃድ መሪ በመሆን እና የተነፋፉ ባሉኖችን የሚይዙ እድሜአቸው ከ13 ዓመት በላይ የሆኑ በጎ ፈቃደኛ ተሳታፊዎች ያስፈልጋሉ። በበጎ ፈቃደኝነት የሚሳተፉ ሰዎች ቅዳሜ፣ ኖቬምበር 18 ሠዓቱ ከ** 7:30 a.m. **እስከ** 1:30 p.m. **(በጎ ፈቃደኞቹ ስድስቱንም ሠዓት መገኘት አለባቸው) ፍላጎት ያላቸው ሰዎች የሰልፍ ትርኢት በሚለው ገጽ ላይ ለመመዝገብ ይችላሉ።**
www.SilverSpringDowntown.com

**የክረምት አየር ሁኔታን ለመከታተል ከMCPS ጋር ሁልጊዜ ይገናኙ፡-**

<Summary:> በአየር ሁኔታ ምክንያት የት/ቤቶችን መዘጋት፣ ዘግይቶ እንደሚከፈት፣ እና ተማሪዎች ቀደም ብለው እንደሚሰናበቱ ለወላጆች እና ለተማሪዎች የትምህርት ሥርዓቱ የሚያሳውቅበት በርካታ መንገዶች አሉት። ሁልጊዜ ወቅታዊ ማስታወቂያ/ኢንፎርሜሽን እንዴት ለማግኘት/ለማወቅ እንደሚችሉ እርግጠኛ መሆን አለብዎት።

የክረምት የአየር ሁኔታ ተቃርቧል። በአደገኛ አየር ሁኔታ ምክንያት ስለ ት/ቤት መዘጋት፣ ት/ቤቶች ዘግይተው ስለሚከፈቱበት ሁኔታ፣ እና ተማሪዎች አስቀድመው ስለሚለቀቁባቸው ሁኔታዎች፣ ወላጆችን ለማሳወቅ MCPS በተለያዩ መንገዶች ያቀርባል።

- **ከMCPS-ማስጠንቀቂያ** (AlertMCPS)
  ከአየር-ጋር-የተያያዙ የአስቸኳይ ሁኔታዎች እና በት/ቤት ስርአት ተፅእኖ በሚያደርጉ ሌሎች አሳሳቢ ሁኔታዎች ወቅት የቴክስት መልእክቶች ወይም ኢ-ሜይሎችን ከMCPS ይቀበሉ።
  ወላጆች በተለይ የልጆቻቸውን ት/ቤቶች የሚመለከቱ ማስጠንቀቂያዎችን ለመቀበል በኮምፒውተር መመዝገብ ይችላሉ።
  ለAlertMCPS ተመዝገቡ

- **የMCPS ኬብል (ቲቪ) ቻነሎች**
  Comcast 34፣ Verizon 36 ወይም RCN 89

- **የተዘገበ መረጃ**
  301-279-3673

- **MCPSን ይጠይቁ**
  301-309-6277 ሰራተኞች ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ7:30 a.m. እስከ 5:30 p.m በእንግሊዝኛና ስፓኒሽ ጥሪ ይቀበላሉ።

- Twitter
  እንግሊዝኛ (English): https://twitter.com/MCPS
  ስፓንሽ (Spanish): https://twitter.com/mcpsespanol

- Facebook
  እንግሊዝኛ (English): https://www.facebook.com/mcpsmd/
  ስፓንሽ (Spanish): https://www.facebook.com/mcpsespanol/

- **የአካባቢ ሬድዮና ቴሌቪዥን ጣብያዎች**
  የአስቸኳይ ጊዜ መገናኛ መረጃዎች በልጅዎ ት/ቤት ማህደር ወቅታዊ መሆኑን እባክዎ ያረጋግጡ።

  የMCPS አስቸኳይ ሁኔታ መረጃ አቀባበል

**የክረምት ኮት/ካፖርት ዘመቻ ተጀምሯል**

<Summary:> **የቅድመ ሙዋእለህፃናት እና ቀደምት ጀማሪ ህፃናት ጽ/ቤት ለወንዶች እና ለሴቶች ልጆች የሚሆኑ የክረምት አልባሳትን ጃኬቶች፣ ኮፍያዎች፣ የእጅ ጓንቶች የመሳሰሉትን የክረምት ልብሶችን እርዳታ እየሰበሰቡ ናቸው።**

**የቅድመ ሙዋእለህፃናት እና ቀደምት ጀማሪ ህፃናት ፕሮግራሞች እርዳታ እየጠየቁ ያሉት ለተማሪዎች አዳዲስ የክረምት ልብሶችን ለመስጠት ነው።**

**ለወንዶች እና ሴቶች ልጆች የሚሰበስቧቸው ኮት/ጃኬት ቁጥራቸው(ልካቸው)** 5, 6, 6x, 7 **እና** 8 **እና ሌሎችም እንደ ኮፍያ እና የእጅ ጓንት የመሳሰሉትን ያካትታል። እርዳታው የሚላከው በሚከተለው አድራሻ ነው፡-** Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Room 141, Rockville, MD 20852.

**ለተጨማሪ መረጃ** Lisa Conlon (**ሊዛ ካኖን**) **በስልክ ቁጥር** 301-230-0676 **መጠየቅ ይችላሉ።**